# *የደህንነት ሰውየውና ምጥን ተግባሮቹ*

# *በዱባይ*

## ከታደሰ ደስታ

## ክፍል - አንድ

ለዚህ ጽሁፌ መነሻ የሆነኝ አንድ ጸሓፊ ከጥቂት ወራቶች በፊት በድህረ ገጾች ላይ ኢትዮጵያዊያንና ቆንስላቸው በዱባይ በሚል ረዕስ ያስነበቡን ጽሑፍ ነው፡፡ ጸሓፊው በራሳቸው ዕይታ ያስተዋሉትን በተለይ ስለ ኢትዮጵያ ጀነራል ቆንስሌት ወቅታዊ ሁኔታ ሰለአሰራሩ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ከሞላ ጎደል ዳሰው አሳይተውናል ፡፡ ሆኖም እንደዚህ ጽሑፍ አቅራቢ እምነት ያ ጽሑፍ ሙሉ አልነበረም ፡፡ በተለይ ጽሑፉ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ሁለት አንኳር ነጥቦች ያልተጠቀሱ በመሆኑ እነዚህኑ አብይ ነጥቦች እንደወረዱ በገሃዱ እይታ ይዤ በመቅረብ የበኩሌን እነሆ እላለሁ ፡፡

በመረጃ ባለሙያነት ለማገልገል ከማንኛቸውም ተፈላጊ ነገሮች ሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጠንካራ ሥነ-ምግባርና በራስ የመተማመን ብቃት ነው ፡፡ በሥነ-ምግባርና በመረጃ አያያዙ ደካማ የሆነን የመረጃ ባለሙያ በስለላ ስራ ላይ ማሰማራት ውጤቱ ሰላዩን እራሱን ለሌላው ወገን የጥቃት ሰለባ እንዲሆን ማመቻቸት ማለት ነው ፡፡

በዘመናችን ለመረጃ ሥራ ስኬት የሆኑትን የቴክኒዎሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ወይንም በለቀማና የእግር ለእግር( Manual ) የክትትል ሥራ ላይ የመረጃ ሰራተኞች የግል የሥነ-ምግባርና ሙያዊ ብቃት(skilled) ወደ ተፈላጊው ግብ የሚያደርሱ መረማመጃዎች መሆናቸው አጠያያቂ አይደለም፡፡

ለዚህም ነው መንግስታት በመረጃ ክትትል፣ ማሰባሰብ እና ትንተና ላይ አጅግ የሚደክሙትና ለግምት የሚያስቸግር በጀት ሲያፈሱ የሚታዩት፡፡ የተሳለጠ እጅግ ዘመናዊ የመረጃ Network ( ግንኙነታዊ መረብ ) በመዘርጋት መረጃን የሚያሰባስቡት ፡ምዕራባዊያን እንኳን ከሁሉ በፊት ላቅ ያለ ጊዜና ዋጋ የሚከፍሉት በእያንዳንዱ የመረጃ ሰራተኞቻቸው የስነ-ምግባርና የግል ሕይወት ዙሪያ ነው ፡፡ ምክንያቱም የመረጃ ሠራተኞች በስራቸው አጋጣሚ በእጃቸው በሚገቡት ጥብቅ ሚስጥሮች መነሻነት አንዳንድ ጊዜ ከሚፈለጉት ባለ ጉዳዮች ( Object ) ጋር በስውር በመደራደር የግል ብልፅግናን ለመፍጠር ስለሚጠቀሙበት ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ ክፍተት በተለያዩ ሀገሮች በተለያየ ጊዜ ሲፈጠር እንደ ነበረ ማስረጃ መዘርዘሩ ጊዜን ማባከን ነው ፡ በተለይ በአፍሪካ ለመንግስታት የደህንነት ቢሮ ተቀጥሮ መስራት በራሱ የሚፈጥረው የተለየ ዕድል ምክንያትነት ከድህነት ለመሸቀንጠርና ወደ ተሻለ የኑሮ ኮርቻ መፈናጠጫ ዕርካብ ተደርጎ ስለሚታይ ከእውነተኛው የመረጃና የ( Intelligence ) መርሆዎች ( Ethics ) እጅጉን ባፈነገጠ መልኩ የግል ብልጽግናን ለማምምጣት ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል፡፡ለዚህም ነው በአፍሪካ ዜጎች ሁልጊዜ የደህንነት አባላቶችን በጥርጣሬና በፍራቻ እንዲያዩ የሚገደዱት ፡፡

በየአካባቢው የግለ-መንግስትነት (Local Government) ሥርዓትም የሚፈጠረው እንደዚህ ካለው የግለሰቦች በየአካባቢያቸውና በሚያውቁዋቸው ሰዎች ዘንድ ገዝፎ ከመታየትና ከመፈራት ከሚመነጭ አዙሪት ነው፡፡በታሪክ ክስቶች ደጋግመን እንዳየነው እነደዚህ አይነቱ ግለሰባዊ አንባገነንነት ስርዓት ማቆጥቆጥ ቀስ በቀስ ስር እየሰደደ ለዋናው ሥርዓት መበስበስ ላቅ ያለ እርሾ ይሆናል ፡፡

እኔም ለዚህ የመግቢያ መንደርደሪያ የሆነኝን ባጭሩ እንዲህ ካልኩ ወደ ዕለቱ ተያያዥ ርዕስ ለጥቂት ጊዜ ቆይታ አብረን እንድንዘልቅ እጋብዛለሁ፡፡

በዱባይ የኢትዮጵያ ቆንስሌት ጽ/ቤት የደህንነት ባልደረባና በመላው መካከለኛው ምስራቅ የኢትዮጵያ የደህንነት መ/ቤት ተወካይ ነኝ ባዩ ግለሰብ ላይ ባሰባሰብኳቸው ማስረጃዎች መሰረት ለግንዛቤ ያክል እንዲረዳን በዚህ በክፍል አንድ በጥቂቱ ጨለፍ እያደረግን የመጀመሪያ ዙር የዳሰሳ ቅኝት እናደርጋለን ፡፡

ይህ ግለሰብ ዱባይ ላይ ከተመደበበት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በተለይ ለጥቅም ጥያቄ የሚፈልጋቸውና ደህና የንግድ እንቅስቃሴ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ጋር ሲገኝ « ጌታቸው እንዳለኝ፣ጌታቸው እንዳዘዘኝ ወዘተ በሚል የንግግር መክፈቻው ይታወቃል ፡፡

እንዲህ አይነቱም መልዕክት የርሱን በበላዮቹ ዘንድ ያለውን ተደማጭነት በማሳየት በሌሎች እንዲፈራ የሚጠቀምበት ደካማ ስልቱ ነው ፡፡መቼም የአንድ ሃገር የደህንነት ሚኒስትር ዕታች ወርዶ ከመዋቅር ውጭ ለአንድ ተራ የደህንነት አባል መመሪያ እንደማይሰጥ መገመት የተለየ እውቀት አይጠይቅም ፡፡

ግና በዱባይና በአቡዳቢ በስማቸው የሚነገደው የኢትዮጵያው የደህንነት ሹም ስማቸው ከአዲስ አበባ ከሚመጡ የተለያዩ የመንግስት ዕቃዎች ገዢዎች ላይ ፈርቅ ( Commission ) ጣሪያ ለማጨመር ያልዋለበት ጊዜ የለም፡፡

እንደሚታወቀው ዱባይ በንግድ እንቅስቃሴዋና ነፃ የገንዘብ ዝውውር (Free Money Import Export ) ፖሊሲዋ ምክንያትነት (በነገራችን ላይ በዱባይ ማንኛውም ሰው የፈለገውን ከረንሲ በፈለገው መጠን በካሽ ( Liquied cash ) ወደ ሃገሪቱ ይዞ መግባትም ሆነ መውጣት በህግ ይፈቀድለታል፡፡ የሚጠበቅበት ሲያስወጣና ሲያስገባ ማስመዝገብ (Declare )ማድረግ ብቻ ነው፡፡)በዚህ ምክንያት ከአለም ዙሪያ የብዙሃኑን ቀልብ በመሳብ ዋና የንግድ ማእከል ለመሆን ከበቃች ሁለት አስርት ዓመታትን አስቆጥራለች ፡፡

በመሆኑም ነው በዚህ ዓይነቱ ንግድ ስበት ላይ ከከፍተኛ እስከ መካከለኛ የአስመጪነት ንግድና የኮንስትራክሽን ሙያ ተቋራጭነት ላይ የተሰማሩ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ባለሃብቶች እንደነገሩ ተሳታፊ መሆን የቻሉት ፡፡

በተለይ በሃገራችን ካለው የወጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ለሚዛባው የንግድ ሚዛን ማስተካከያ ነጋዴዎቹ በግላቸው እያሳደዱ የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ ፤ ግዢ ወደ አከናወኑባቸው ሃገሮችና ኩባንያዎች ክፍያ ለማስተላለፍ (በባንክ ተፈቅዶ በ LC ወይም በ CAD በግልፅ ከሚተላለፈው ወጭ ማለት ነው ) ተቀማጭነታቸው ዱባይ የሆኑትንና ድርጅትነታቸው የኢትዮጵያዊያን የሆኑትን የሃዋላ ድርጅቶች(ግለሰቦችን) የሚጠቀሙት፡፡ድርጅቶቹ በአሜሪካ አውሮፓና ኤዢያ ታላላቅ የንግድ ከተሞች ቅርንጫፍ ቢሮ ስላላቸው የግዢ ሂሳብ ክፍተትን ከእነርሱ ከሚገኝ ዶላር ማሟላት የተለመደ ተግባር ሆኗል ፡፡

እንግዲህ እነዚህ ድርጅቶች ናቸው የደህንነቱ ሰውዬ የግል ሰለባ የሆኑት ፡ « ለአልሸባብ ለአነግ ገንዘብ ታስተላልፋላችሁ እያለ እንደየ ሁኔታውና የሃገር ውሰጥ የፖለቲካ ሰሞነኛ ወሬ አርእስቱን እየቀያየረ በማስፈራራትና እንቢ ካላችሁ አዲስ አበባ ያሉትን ወኪሎቻችሁን ከነ ገንዘባቸው አሳፍሳቸዋለሁ በማለት ቋሚ ምንደኛ ሆኖ ህገወጥ ጥቅም የሚሰበስበው ፡፡ እጅግ የሚያስገርመው ግን ራሱ ግለሰቡ በዘረጋቸው ሥውር መረቦች አማካኝነት ህገ-ወጥ ገንዘብን በተለያየ መልክ ህጋዊ ስራ ውስጥ በማስገባትና በማዘዋወር ሥራ (Money Laundering) ውስጥ እሰከ አንገቱ መዘፈቁ ነው ፡፡

በሌላም በኩል የምስራቅ ኢትዮጵያ የሶማሌ ክልል ተወላጆች በተለይ ለዋናዋ ሱማሊያ ከሚያዋስኑት የድንበር አካባዎች እንደነ ቦህና ጋላዲን ዋርዴር ከመሳሰሉት የድንበር አካባቢዎች የሚመጡ በርካታ የኢትዮጵያ ሶማሌዎች፣የዋናዋ ሶማሊያ (ሞቃዲሾ)፣ የሶማሌ ላንድና የፑንት ላንድ የንግድ ማህበረሰብ በዱባይ ከየትኛውም የአፍሪካ አካባቢ ከሚመጡት ነጋዴዎች በበለጠና በተደራጀ መልኩ በከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በመታገዝ ወደ ምሰራቅ አፍሪካ አካባቢዎች ከፍተኛ የንግድ (Empire) በመመስረት ይንቀሳቀሳሉ ፡፡

ለዚህም ማረጋገጫ ደግሞ ዱባይ( Dubai Creek Port ) እና ሻርጃ ( Kahalid Port ) መመልከቱ በቂ ይሆናል ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም ከላይ የተገለፁትና በኩታ ገጠምነት ከሱማሊያ ጋር ከምንዋሰንበት ድንበር አካባቢ የሚገኙ ዜጎች እንደ አየሩ ሁኔታና የፖለቲካ አካሄድ በፈለጉ ጊዜ ኢትዮጵያዊ ፤ ሲያሻቸው ደግሞ ሶማሌያዊ የመሆን እድላቸው ከአካባቢው ፖለቲካ ተነሳ የተመቻቸ ስለሆነ በትክክል ኢትዮጵያዊውን ለመመዝገብና ለመለየት እጅግ አዳጋች ነው ፡፡

በተለይ በሶማሊያ ፓስፖርት ወደ ዱባይ ከገቡ በኋላ ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍል ለንግዳቸው እንደልብ ለመንቀሳቀስ የኢትዮጵያን ፓስፖርት መያዝ ስለሚፈልጉ ይህ ደግሞ ዱባይ ላይ በቀላሉ በደህነቱ ሰውዬ በኩል ( Approval ) ማረጋገጫ ከተሰጠ በእጅ ሊገባ ስለሚችል የሚጠየቀው ስውር ክፍያ ተከፍሎ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ማግኘት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ፡፡

እንዲያውም ሰውየው በማን አለብኝ ከልካይ ስሜት ይህን ያክል ብትከፍሉ ፓስፖርቱን በዚህን ጊዜ ውስጥ ከአዲስ አበባ አስመጣላችኋለሁ የአገልግሎት ጊዜውን ለጨረሰ ( Expired ) ላደረገባችሁ አድስላችኋለሁ በማለት በስውር ወኪሎቹ በኩል ይደራደራል ፡፡

በሌላም በኩል በዱባይ ከተማ በርከት ያሉ የኢትዮጵያዊያን ሬስቶራንቶች ፤ኮፊ ሾፖችና የምሽት ክለቦች ይገኛሉ ፡ አብዛኞቹ የነዚህ ድርጅት ባለቤቶች ደግሞ ከዚሁ የደህንነት ሰውዬው የአይን ግልምጫና ጥቅሻ አላመለጡም ፡፡

የሰውየው በድርጅታቸው ውስጥ አዘውትሮ መታየት በደንበኞቻቸው ላይ ተፅዕኖ ስለሚያመጣ የዚህ ፍራቻ ደግሞ በተቻለ መጠን ሰውየውን በእጅ መንሻ መያዝ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል በየጊዜው እንደ ድርጅታቸው ብዛት ገንዘብ እየተመዳደቡ እንደ የወር ደሞዝተኛ ገንዘብ ለማሰባሰብና ለመስጠት የሚገደዱት፡፡ በእርግጠኝነት ግን የግለሰቡ ወሬ ለመለቃቀም እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰፈር መገኘት « መረጃ አይናቅም አይደነቅም » የሚለውን የቆየ የደህንነቶች አሰራር ምክንያትነት እንዳልሆነ መገመት እንችላለን ፡፡

ቆንስላ ጽ/ቤቱ ከተከፈተ ጀምሮ በቋሚ ርስትነት ለተከታታይ ረጅም ዓመታት ዱባይን እንደ ግል ይዞታው ስለተቆጣጠረውና በኢትዮጵያዊያኑም ዘንድ ይህ ጉዳይ የፈጠረውን ገጽታ በመጠቀም (በማጉላት) የበላይ አለቆቹንም የቀጥታ የጥቅም ተካፋይ በማስመሰል በየጊዜው በሚፈጥራቸው የገንዘብ መጠየቂያ አርዕስት እንደ ጥያቄው በስውር ገንዘብ ይዋጣለታል ፡ እንደውም አንዳንዶቹ ዜድ ቴሌቶን (Z Telethon ) እያሉ በስላቅ ይጠሩታል ፡፡

ለአብነት እንኳን ባለፈው ዓመት መጨረሻ አካባቢ ሴት ልጁን ወደ ካናዳ ልኮ የሚያስተምርበትን የኮሌጅ ክፍያና ሽኝት በማስመልከት የተደረገው ቴሌቶን የሚጠቀስ ነው ፡፡

ከሁሉም በላቀ ደግሞ የጋብቻ ሰበዙን በመምዘዝ « የኃየሎም አማች ነኝ » የሚለው መፎከሪያው በብዙዎች ዘንድ ለመፈራትምና ከርሱ ጋር ብንጋጭ መዘዙ ብዙ ነው ፣ ሃገር ቤት ለመሄድ እንቸገራለን፣ በሃገር ቤት ቢዝነሳችን ላይ ችግር ይፈጠርብናል ፡፡ሰውየው ጥሩ መከታ ስላለው ነው ይህን ዓመታት ያክል ያለ ተቃውሞ የሚሰራውን ስራ እያዩ እየሰሙ ዝም የሚሉት፤ እውነትም እርሱ እንደሚለው ከአለቆቹ ጋር ጥብቅ የጥቅም ግንኙነት አለው » ብለው በጥርጣሬም ቢሆን ለማመንና ለመቀበል የተገደዱት ፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ከአንዳንድ ነጋዴዎችና የካርጎ ባለቤቶች ጋር በስውር በመመሳጠር «ለደህንነቱ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ የሚላኩ እቃዎች ናቸው » የሚል ሽፋን እየተሰጣቸው እየታሸጉ ተልከው ቀረጥ ሳይከፈልባቸው አዲስ አበባ የሚገቡ ኮንቴይነሮችም እየተበራከቱ ነው ፡፡

እንግዲህ በደህንነቱ መስሪያ ቤት ሽፋን በሚደረጉ ዘረፋዎች ምንጭነት ነው በአዲስ አበባና ክልሎች ላይ ከሁለትም ሶስት የመኖሪያ ቪላና የንግድ ድርጅቶች ባለቤትነት ለመሆን የተቻለው ፡፡

እንግዲህ ጌታቸው እስካለ ድረስ ከዚህ ቦታ የሚነቀንቀኝ የለም በማለት ለሚቀርቡት ሰዎች እንደቀልድ የሚያወራው የዋሁ ደህንነት ሰውዬ በፖለቲካ ትግል ውስጥ ቋሚ ቡድን እንጂ ቋሚ ተሰላፊ ያለመኖሩን አልተገነዘበም ፡፡

በመጨረሻም ከበቂ በላይም ከተበላ ማቀርሸቱ (Regurgitate) አይቀርምና ይታሰብበት፡፡

እያልኩኝ ወደሚቀጥለው አርዕስት እንሻገር ፡፡

በአባይ ወንዝ ላይ ስለሚገነባው ግድብ እኔ በበኩሌ በመሰረተ ሃሳቡ ላይ ተቃውሞ የለኝም ፡፡

እንዲያውም ለኔ ይህ ጉዳይ ቀስቃሽ (Sensationl) ነው ፡፡ አንድ ግድብ አይደለም በአባይ ገባር ወንዞችም ላይ ጭምር በርካት ግድቦች ተሰርተው ለሃገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅም ውሎ ማየት እንደ ዜግነቴም የምደሰትበትና ለዚህም የምችለውን ለማድረግ ወደ ኋላ የማልል ነኝ ፡፡ ሆኖም ይህ የአንድ አባይ ግድብ ቦንድ ግዢ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ስሙንም መጥራት የሚያሰቅቀን የግዴታ የቤት ስራችን እንዳይሆን በፍቅርና በባለድርሻነት በራሳችን ተነሳሽነት የአቅማችንን የምንረባረብበት ውዴታችን መሆን ይገባል ፡፡

በዱባይ ቆንሲሌት ጽ/ቤት ባሁኑ ጊዜ የሚታየው ቅጥ ያጣ ሽርጉድ (Sembalance) ቤቱን የቦንድ መሸጫና መግዢያ (Stock Market ) አስመስሎታል ፡፡

በየቀኑ ነጋዴዎች እየታደኑ ወደ ጽ/ቤቱ ይጠራሉ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ቦንድ እንዲገዙ ይጠየቃሉ፣

በሌላም በኩል ወደ ጽ/ቤቱ ለሌላ አገልግሎት እግር ጥሎአቸው የሚመጡት ባለጉዳዮች ሁሉ በቅድሚያ የሚጠየቁት ቦንድ ገዝተዋል ወይ ነው ፡ ይህንን ጉዳይ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በወቅቱ ማስተካከያ ካልሰጡበት የቆንስላው ጽ/ቤት አገልግሎቶች ሁሉ እንደ ኮሚኒቲው የግዴታ አባልነት ከቦንዱም ግዢ ጋር በቀጥታ እንዳይያያዝብን እንሰጋለን ፡፡ እንደዚህ ያለው ልምምድ ደግሞ ምናልባት ቆንስሌቱ እንዲሰበስበው የተሰጠው ኮታ ለማሟላት ሩጫ ካልሆነው በስተቀር የትም አያደርስም ፡፡ ስለዚህ ቦንድ አንዳንዴ እንደሚባለው «ቦንብ ሆኖ እየፈነዳ (ከአቅም በላይ እየተጠየቅን )እንዳይጎዳን አጠማመዱ ላይ ማስተካከያ ይሰጥልን ፡፡

እኛም በዜግነት የምንለው ይሰማልን ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታልና ፡ የአንድ ወገን ብይን ይቁምልን በምክክርና በመግባባት በፈቃደኝነት እናድርገው፡፡ በሙከራ ደረጃም (Probation) እየተሰራብን ከሆነ የአቅም መለኪያ መስፈርት ይውጣልን ፡፡

እንዲያው ነገር ነገርን ያነሳውልና የትናንቱ «**<u>ገለልተኛ</u>** » የዛሬው ቆራጥ አብዮተኛ ክቡር ጀነራል ቆንሲላችንም እንደትናንቱ በአዲስ አበባ ባለ አደራ ቦርድ ጊዜ ገለልተኛ ተብለው ተሰይመው የፖለቲካውን ቁልፍ በስውር በጠረጴዛ ሥር ከበረከት ስምኦን ተቀብለው የጀግናውን የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ፖሊሲ ሲያስፈፅሙ እንደነበረ ያደባባይ ሚስጥር ቢሆንም ፤ዛሬ ደግሞ በሴት እህቶቻችን ላይ በዚህ ሃገር የሚደርሰውን በደል እያዩ ገለልተኛ ነኝ እንደማይሉ ተስፋ አለን ፡፡

የጽ/ቤት ህንፃን መቀየርና በርካታ ሰላይ ዲፕሎማቶችን መጨመር በራሱ ለውጥ አያመጣም ፡፡

ለድርጅትና ለመንግስት ወገንተኛ መሆን ብቻም በራሱ የትም አያደርስም፡፡ምናልባት ያሾም ያሽልም ይሆናል፡፡ይህ ደግሞ ማንም የትኛውንም ሥርዓት በቁርጠኝነት ቢያገለግል ሊደርስበት የሚችለው የዕድገት ደረጃ ነው፡፡ ግና ለአረብ አገር ቁርጠኛና ለወገን ተቆርቋሪ እንዲሁም በቂ የስራ ልምድ ያለው ዲፕሎማት ያስፈልገናል ፡፡ ለነገሩ በቅርቡ ከተጨመሩት ዲፕሎማቶች መሃከል በምክትል ጀነራል ቆንስልነት የተመደቡት ግለሰብ በተለይ በቤይሩት ይሰሩ በነበረበት ወቅት የእህቶቻችን መብት ለማስከበር ከሊባኖስ መንግስታት ጋር ያደርጉት የነበረው ዲፕሎማሲያዊ ትግልና ያስገኙትን መለካም ውጤቶች እዚህም በዱባይ ይደግማሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ለነገሩ እንደነዚህ አይነት ውስብስብ ችግሮች በአንድ ጠንካራ ዲፕሎማት ጥረት በአንድ ጊዜ የሚፈታ ሳይሆን መንግስት በፖሊሲ ደረጃ ሊያስተካክለው የሚገባውና በተለይ መንግስት በመካከለኛ ምስራቅ ላይ ያለው ( Strategy ) እንደገና ሊጤን የሚገባው ነው ፡፡ እንዲያውም በቅርቡ በምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የሚመራው የልዑካን ቡድን ዱባይ ላይ ኮሚኒቲውን ሰብስበው ማነጋገራቸውን ተከትለን «ምነው ያን ሁሉ ዘመን ስንጮህ ከርመን ዛሬ ምን የተለየ ነገር ተፈጥሮ ብቅ አሉ ይህች የቦንድ ዜማ ገና ዋናውንም ሳታመጣልን አትቀርም ብለን በትዝብት አልፈናል ፡፡ ለነገሩ ዋናውም ቢሆን በፊት በፊት ጊዜ ከአነግ ጋር ለመደራደር እግራቸው እሰኪቀጥን ድረስ እዚሁ ሲመላለሱ እንደነበረ እራሳቸው በአንድ ወቅት በፓርላማ ላይ ሲናገሩ ሰምተን የለ !! ግና ምን ዋጋ አለው ታዲያ አንዴም እንኳን ሰብስበው ሊያናግሩን አልሞከሩም፡፡

ግን ግን አሁን ተስፋ አለን ፡፡ ስለ ቦንዱም ብለው ሊያነጋግሩን ይችላሉ፡፡ መቼም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ከደም ውህደት እንዲሁ በቀላሉ ቶሎ አይጠራምና ፤ እዚህ የምንገኘውን ኢትዮጵያዊያን በሙሉ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መነፅር ለማየት እንዳይቸገሩ አደራ እያልኩ፣ አንዳንዴም የህዝባዊ ዲሞክራሲን ጐግል ይዋሱ እንላለን ፡፡ ምክንያቱም እንደ ዜግነት ከቆንስላው ጽ/ቤት ማግኘት የሚገባን አገልግሎት በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መርህ መሰረት ለወገንተኛ ብቻ የሚሰጥ አገልግሎት እንዳይሆንብንና ዛሬ በምልክት ደረጃ እየታዩ ያሉት አዝማሚያዎች ነገ ወደ ቦንዱ ግዢ ያድጉና « ቦንድ ያልገዛ አይስተናገድም » ወደ መባል ደረጃ እንዳንደርስ ስለምንሰጋ ነው ፡፡ እንግዲህ በክፍል አንድ ዳሰሳ ይህን ያክል አብረን ከተጓዝን ከመለያየታችን በፊት ግን ሰሞኑን በየክልሎቻችን ፕሬዘዳንቶች ቢሮ እየተካሄዱ ያሉት ስሜት ሰጪ፤አስደንጋጭ የካቢኔዎች ግምገማ ላይ ( Lose )ለሚያደርጉትም ሆነ( Gain )ለሚያደርጉት ሁሉ መልካሙን እየተመኘሁ ፤ አንዳንዴ ሳይታሰብ እየገነፈለ የሚያቃጥል የፖለቲካ ግምገማ ሰክኖ እስኪበርድ ድረስ ሰለባ ወይንም ጭዳ ለሚሆኑ ሁሉ ጽናቱን እየተመኘሁ እሰናበታለሁ ፡፡

tadessedesta32@yahoo.com